# ሕዝብና ጦርነት መግደልና መሞት

አብርሃም በየነ

ጦርነትና ሰላም የመጠላላትንና የመፈቃቀርን ያክል ዕርቀትና ቅርበት ይዘው የሚጓዙ ሁነቶች ናቸው። ሰላም የጦርነት ማህደር ነች። ጦርነት ግን ከሰላም ጉያ ያፈተለከ ቋያ እሳት ነው። ሳር ቅጠሉን የሚለበልብ። ተራራውን የሚደረምስ። ሜዳውን በሬሳ የሚያልከሰክስ። ረባዳውን በደም ኩሬ የሚያጨቀይ። አየሩንም በተውሳክ የሚበክል ኩነት ነው። ሰላም የሰከነች ጦርነት ነች። ባንፃሩ ጦርነት ግን ጨርቁን የጣለ ሰላም ነው። ስለጦርነት ሲታሰብህ ቀድሞ ወደ ህሊናህ የሚመጣው ህዝብ ነው።

ጦርነት ሕዝብ ነው። ሕዝብም ጦርነት ነው። ገዳዩም ሰው። ተገዳዩም ሰው። በሁለቱም ወገን የሞት ሰለባ የሚሆኑት የሕዝብ ልጆች ሆኑና ጦርነትን ህዝብ አደረጉት። ገዳይና ተገዳይም ሆነው ህዝብን ጦርነት ሊያደርጉት ቻሉ። በየትኛውም ወገን ሆነህ ተመልከተው፤ ጦርነት ሁለት መልክ ነው ያለው። ጥቁርና ነጭ። ግማሽ ቀለም የለውም። ቡላ፤ ግራጫ፤ ወይም ቀይ ዳማ ቀለም የለውም። ወዳጅና ጠላት ነው። ጠላት የሞትን ፅልመት ሳቢ። ወዳጅ ደግሞ የመኖር ኢጋር ሆነው ያለ አንዳች ብዥታ ይታዩሃል። በጦርነት በህይዎት የመኖር ዋስትና ሰጪ መግደል ስለሆነ ላለመሞት ቀድመህ ትገድላለህ። ማሰብ የለም። ማሰብ ማወላወልን ይወልዳል። ብሎም ሞትን። በጦርነት ወቅት ጠላት መልክ የለውም። አውሬ ነው። ጭራቃዊ ሰይጣን። በጦረነት ወቅት ለመሰንበት በርካታ ህግጋትን ትሽራለህ። ዓለም የቆመችው ለውሸት እንጂ ለዕውነት ስላልሆነ ሃቅ ዕድሜ አይቀጥልም። እናም ስለ ሞራል ስልጣን አትጨነቅም። ዓላማህ ጠላትህን በጦር ስልት አታለህ ድልን ያንተ ማድረግ ብቻ ስለሆነ ጠላትህም ስላንተ ሰብዕና አይጨነቅም።

በጦርነት ወቅት ቀድሞ ወደ ህሊናህ የሚመጣው ሕዝብ ነው። እኛ፤ ጓደኞቼ፤ ውንድሞቼ፤ ጓዶቼ፤ ወገኖቼ፤ . . . . ሁሉም ባንድ ተቀናጅተው ተሰፋው የደበዘዘ ህይዎት ሲኖራቸው በጦርነቱ ውስጥ ጨልመው ይመጡብሃል። ልታያቸው ሊያዩህ ይችሉ ዘንድም ሻማ ልትሆንላቸው ትቆርጣለህ። ስትቆርጥም ሰብዕናህን ትፍቅና ወደ አራዊትነት ትለወጣለህ። ፊት ለፊትህ የተሰለፈው ጠላትም እንደ አንተ ሰው መሆኑን ባትረሳም የምትገድለው አካል ግን  ሰው ሆኖ አይታይህም። ጠላት ነው። ሞትህን የሚለግስህ፤ መኖርህን የሚነሳህ "አራዊት" ነውና ሳይቀድምህ ለመቅደም ቃታ ትስባለህ። በግዳይህ ሃሴትን ተጎናጽፈህ ደሙን ስትረጭ፤ ህይዎቱን ስታጠፋ ጀብዱ እንጂ ሃዘን አይሰማህም። ይልቁንም ትጀግናለህ። ሳታውቀው በድርጊትህ እርካታ የራስህን ሰብዕና ራስህ ትፍቀዋለህ። በምትኩም የአራዊት ባህሪይ ይዋረስሃል።

በጦር ግንባር ተሰልፈህ ራስህን የምትመለከተው እንደ ጥሩ ሰው (we are the good guys) ሌላውን ግን እንደ መጥፎ ሰው (the are bad guys) ስለሆነ በምታጠፋው ህይዎት አትፀፀትም። በጦር ግንባር ተሰልፈህ የጠላትህን ሰው መሆን ያሰብክ ቅጽበት ሞትህን ትጠራለህ። ሰልፍህ ወይ መግደል ወይ መገደል ስለሆነ በዚያች ቅፅበት ራስህን ሰው ለማደረግ አንተውን አታሞኝም። በሁለቱም ተፋላሚዎች ህሊና ያለው ቅፅበታዊ እሳቤ አንድ ዓይነት ነውና ቀድሞ ጠላቱን በመግደል ቅልጥፍና ያገኘው ወገን የህይዎቱን የመሰንበት ክርር ያስረዝማል። በዚህ መልክ ሁሉም እስከ ጦርነቱ ፍጻሜ ራሱን ሰው አድርጎ ላለማየት አራዊትነቱን እንደለበሰ በጦርነት እሳት ይለበለባል።

በጦርነት ወቅት ሰው የመሆን ስብዕና በወታደረነት ይለወጣል። የመቁሰል፤ የመማረክ፤ የመጥፋትና ሌሎቹም የሰቀቀን ዓይነቶች በጀብዱ ታጅለው ስቃይህን በፀጋ እንድትቀበለው ያደርጉሃል። ምንም ይሁን ምን ማማረር በጦረነት ወቅት ቦታ የለውም። የወከልከውን መንግሥት ወይም ቡደን (ፓርቲ) በድል እንጂ በሽንፈት ልትወክለው ስለማትሻ በሚደርስብህ ስቃይ የሚሰማህን ህመም (pain) ችለህ ውጊያው እስኪፈጸም ህመምህ የቁንጥጫ ያክል እንኳ እንደ ተሰማህ ከፊትህ ላይ አታስነብብም። ቆስለህ መራመድ ከቻልክ ወደፊት እንጅ ወደ ኋላ አዞረህ አትመልከትም።

ወታደር ነህ። የጦር ማገዶ። እናም በባሩድ አሩር ትቆላለህ። ባዙቃና መድፍ አያጓሩ ቦቃ እሳት ሲተፉ፤ የመሸግህበት ጉድብ ይዞህ ሲደረመስ ዘልለህ ከምሽግህ ትወጣና በፈንጂ እሳት ውስጥ ትቆሰቆሳለህ። አካልህ የጨርቅ ቅዳጅ እስኪ መስል ይበጣጠሳል። ከሰውነትህ አንደኛው ክፍል በመድፍ ተጠርቦ ካንተ ይነጠላል። ጓድህ አንጀቱ ተዘርግፎ የሆድ ዕቃውን በዕቅፍህ እንድትይዝለት ጓዳዊ ፍቅሩ ያስገድድሃል። በዚህ መንገድ ነው የተፈጥሮ ፍርሃትህን ከራስህ የምታወርደው። ሞትም ባልንጀራኑቱን በይፋ የሚገልጽልህ ይኼኔ ነው። የሰው ልጅም በእድሜ ዘመኑ ሲኖር ከጎኑ ተነጥሎት የማያውቀውን ሞትን በቅርበት የሚያውቀው በጦርነት ወቅት ሳይሆን አይቀርም። በጦርነት ወቅት ሳትወድ በግድ ከሞት ጋር ትጎዳኛለህ። እርሱም እስከሚከዳህ ድረስ አብሮህ ውሎ አብሮህ ያድራል። የካዳህ እለት ግን ሞትክ ትባላለህ።

ሰው መሆንህ በወታደርነት ተለውጧልና የስርዓቱ ወይም የፓርቲው መሳሪያ ነህ። እኔነትህ (ግለሰብነትህ) ተፍቋል። በጦዘ ጦርነት ውስጥ ሳታውቀው የሃዘን ቲያትር ተዋናኝ ሆነሃል። የጦር ሜዳው ግንባር ተውኔትህ አድናቆትን ይቀዳጅ ዘንድ ጅብዱህን ታሳይበታለህ። ግን አስበኸው አይደለም። ጦርነቱ ነው የወለደው። ጥይት በጆሮህ እያፏጨ መትመሙን ሲቀጥል የሚመታህና የሚገድልህ ሆኖ ሳይሆን የሚሰማህ የመድረኩ የሙዚቃ ቅንብር ሆኖ ነው። ፀጉርህን ያቆመዋል። በባሩድ ሃሩር የደረቀው ላንቃህ የውሃን መኖር ይረሳዋል። ሃሞትህ እንደ ጀበና ቡና ሲንተከተክ መሃል ራስህን ይነዝርሃል። በዚህ ጊዜ የት የሌለ ሀይል በሰውነትህ ይዘራና የጠላትህን ሀይል እንድትንቀው ህሊናህን ያውረዋል። አፍንጫህን የሰናፍጭ አዋዜ የባላህ ይመስል ይሰረንቅሃል። ልብህ ትርታውን ሲደቃ የአታሞ ንረት እስኪ መስልህ ለራስህ ይሰማሃል። ይኼኔ ነው ሞትን የምትንቀው። ልታሸንፈውም እንድምትችል የልብ ልብ የሚሰማህ በዚህች ቅፅበት ውስጥ ስለሆነ ከጠላትህ ጋር ተቀላቅለህ የጨበጣ ውጊያ ውስጥ ትገባለህ።

በጥላቻ ውችንፍር ሰውነትህ ስለተሶረፈ በረፈረፍከው የጠላት ሬሳ ትረካለህ። ሰው መሆንህን ተረሳውና በሞተው አካል ትመጻደቃለህ። በጦርነቱ መቋጫ ላይ አለመሞትህን አረጋግጠሃልና የድልህ ሰርፅ በአከርካሪህ አሸንዳ ወደ እግርህ ሲንቆረቆር ይታወቅሃል። ስብዕናህ በዚህ ሁሉ የስሜት ማዕበል ታጥቦ ሲጎርፍ ግን  ውጊያ ላይ መሆንህን ትረሳዋለህ። ሰው ሆነህ በሰው ፍጥረት ላይ ጭካኔ መፈፀምህንም ልብ አትለውም። የገደልከው ግን ሰው ነበር። አንተ ግን እሬሳ እንጂ ሰው እንዳይባል ገድለኸዋል። ጠላትህን በመግደልህ ከሞት ተርፈሃልና ለዛሬ ሰው ነህ።

ከቆሰልክም ሰው የመሆንህ ጉዳይ  በቁስለኛ ይተካል። እድለኛ ከሆንክ ጓዶችህ ያሸሹሃል። አለያ ግን አንድም የአውሬ ራት አለያም የአሞራ ቀለብ ለመሆን ወድቀህ ትቀራለህ። ከቅጽበት በፊት የጓዶችህ ተከላካይና አጋር የነበርከው ተዋጊ፤ ከቆሰልክ በኋላ ግን የጓዶችህ ሸክም ትሆንና ተቸግረህ ታስቸግራለህ።

በውትድርና ዓለም ውስጥ የአለቃና የጭፍራ፤ የመሪና የተመሪ ልዩነት መኖሩ ዝቅና ከፍ የሚያደርግ የማዕረግ ተባደግን ይፈጥራል። ከድሃ ቤተሰብና ከሃብታም ቤተሰብም የሚምጡ ይኖራሉ። ከፊሉም ወደ ውትድርና ዓለም ወስጥ የገባው የህይዎትን ውጣ ውረድ መቋቋም አቅቶት ያን  የተንዘላዘለውን እድሜውን በጦርነት ሊከረክመው ፈልጎ ይሆናል። ወይም ያለ ፈቃዱ ለግዳጅ ተመልምሎ። አለያም ውትድርናን እንደ ሙያ ቆጥሮ።  ወይም ጦርነቱን የቀሰቀሰው አመክንዮ ሕዝባዊ ዓላማው ማርኮህ ቀኑ የጨለመበትን ሕዝብ የሻማ ብርሃን ልትሆነው ይሆናል ጦርነቱን የተቀላቀልከው። ይህ ሁሉ ግን ወደ ኋላ ቀሪ ክስተት ነው። ጦርነት ይህን ሁሉ ተባደግ በጥይት ዕኩል ያደርገዋል። በጦርነት ታላቁ ዴሞክራሲ ጥይት ነው። ሁሉንም በዕኩልነት ወደ ሞት የሚሸኘው ጥይት ነውና።

በጦርነቱ ፍፃሜ ከእንቅልፍህ ስትነቃ ድርጊትህን በንፅፅር እንዳታይ ትገደዳለህ። ጦርነቱ ያስከፈለውን የህይዎትና የንብረት ዋጋ በትርፍና ኪሳራ ሚዛን መስፈር ትጀምራለህ። በዚህም መስፈርት ውስጥ ሕዝብ የጦርነት ቤተ ሙከራ መሆኑ ጎልቶ

ይታይሃል። በባዮ-ኬምስትሪ ቤተ ሙከራ የሚፈፀሙ ስህተቶች የሚያባክኑት ትንሹ ነገር ቁሳቁስ ሲሆን ከፍ ሲልም ዕንቁራሪትና አይጥ ይሆንብሃል። በማህበራዊ ሳይንስ ቤተ ሙከራ(በጦርነት) ግን አያርሙት ስህተት አይክዱት ዕውነት እንዲሉ የሚጠፋው የሰው ልጅ ክቡር ህይዎት ይሆንና ይሰቀጥጥሃል። ይህም ትግብርትህ የጦርነቱን መነሻ ወደ ኋላ ተመልሰህ እንድትመረምር ይጋብዝሃል። ግን ደግሞ ብዙ ሳትራመድ የፊቱ ወደ ኋላ ሄዶ ስታገኘው ስህተትህን ያስተምሮነት ማካካሻ ልታደርገው ትከጅላለህ። በዚህ መልክ እሳቤህ በህሊናህ ጣራ የሸረሪት ድሩን ሲያደራ የሞት ትርፍ ህይዎትህን ስታስጨንቃት ትኖራለህ።

ህዳር 2006

[abraham3106@comcast.net](mailto:abraham3106@comcast.net)